# ስለ መረቅ

ሰሎሜ መርዕድ

ሰሎሜ መርዕድ ስለ ‹‹መረቅ›› የሰጠችው ሃሳብ እና የአዳም ምላሽ

1. ከሽፋኑ ምስል ከተነሳን ሁለት ጥያቄዎችን ሰንዝሬ አልፋለሁ...

* አዳም ሆይ ይቺ ጥቁር በቀይ ግን አልተደጋገመችም ወይ?

* ምንጯን ወይም የተቀዳችበትን የሆነ መፅሐፍህ ላይ እንደ ዋዛ ሹክ ብለኸን ነበር፡፡ እውን ምንጯ ከወደ የት ነው?

**2. ርዕስ**

ለዚህ በአራት የትረካ አንፃር ለቀረበ ወጥ የልቦለድ መፅሐፍ መረቅ ተስማሚ፣ ተገቢም ርዕስ ይመስለኛል፡፡ አዳም እንደሚለው በ "እንጀራዊ" የአፃፃፍ ስልቱ የተለያየ ስፋትና ርቀት ያላቸውን የእንጀራውን አይኖች የሚያያይዛቸው አንዳች ኃይል አለ... ይኸውም በእንጀራው ላይ የሚፈሰው ወጥ ነው፡፡ በዚህ መፅሐፍ ላይም ቃላት እንደመረቅ እየፈሰሱ ገፀ-ባህርያቱን ለማስተሳሰር ሞክረዋል፤ ተሳክቶላቸዋልም!

ርዕሱን አስመልክቶ ሌላው ያስገረመኝ ጉዳይ በመፅሐፉ ላይ የተለያየ አገባብ ይዞ በተደጋጋሚ መነሳቱ ነው፤ ድግግሞሹ ሲያስገርመኝ ከግማሽ ገፅ በኋላ መቁጠር እንደጀመርኩ ከ20 ጊዜ በላይ መጠቀሱን ለማስተዋል ችያለሁ፡፡

ለምሳሌ፡ ቴቢ መረቁን እንዲህ ተጠቅማበታለች
አላዛር፡ “ቂልነትና ፖለቲካ ከአፌ አስፈንጥሮ የደፋው እሱ መረቅ ... “
ምስክር፡ “ በቀሰም የምትመጠጥ መረቅ ነገር ... “
በምስክር አገላለፅ ደሞ ሐዋሳ ሐይቁ ራሱ ”መረቅ” ነው 🙂

እናም ርዕሱ ለመፅሐፉ እንዳይረዝም፣ እንዳያጥር ሆኖ በልክ የተሰፋ መነን ሆኖ ነው ያገኘሁት! በፈሳሽነት ባህሪውም የተሰጠውን ገፀ-ባህሪያትን የማስተሳሰር ሚና በሚገባ የተወጣ ይመስለኛል፡፡

**3. አዲስ ነገር**

አዳም ከብዙሀኑ የሀገራችን ደራሲዎች በተለየ መልኩ አንደኛ መደብ የትረካ ስልት መጠቀሙ ልዩ የሚደርገው ነገር ቢሆንም ይህንን ችሎታውን በቀደምት ስራዎቹ ላይ በተደጋጋሚ ስላሳየን መረቅ ላይ እንደ ትንግርት ላናነሳው እንችላለን፡፡ እኔን የገረመኝ ግን በአንድ የትረካ አንፃር አልበቃ ብሎት በአራት ዓይኖች (በድምሩ ስምንት ይሆናሉ 😀 ) እንዲሁም በሁለት የፆታ መደቦች ትረካውን ይዞ ብቅ ማለቱ ነው፡፡ አዳም በአባቱ ወንድ፤ በእናቱ ሴት መሆኑን ለድፍን ዓለም ያስመሰከረበት መፅሐፍ ይመስለኛል..... መረቅ! በአንስታይ መደብ ሲተርክ ወላ ‘ሴት ሆኖ ያውቃል እንዴ?’ የሚል ጥያቄን ያጭራል ...

ይህንን የፆታ ልዩነትም ተጠቅሞ አንድን ድርጊት ሁለት፣ ሦስት ዓይነት ስሜትና ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ይህም የደራሲውን የእይታ ስፋት፣ ሚዛናዊነቱንም የሚያሳይ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ቴቢ ያለፈችበትን ጎዳና በቴቢ ጫማ ውስጥ ገብተን እንድናይ ዕድል ባይሰጠንና የቴቢንና የአላዛርን ግንኙነት በአላዛር ተራኪነት ብቻ ቢጠናቀቅ ኖሮ በቴቢ የማይፈርድ ነበር? አላዛርን ስለማፍቀሯ ራሱ እርግጠኛ መሆን ይቻል ነበር? ... በፍፁም! የደራሲውን ሚዛናዊነት እንግዲህ እዚህ ጋር ማስተዋል ይቻላል፡፡

ምሳሌ 2፡- እዝራና ማከዳ በጋራ ስላሳለፉት አንድ ምሽት በየተራቸው ይተርካሉ፡፡ ምሽቱ ለሁለቱም ቆንጆና አስደሳች ነበር፡፡ የደስታችን ምንጭ ብለው የሚገልፁት ድርጊት ግን ለየቅል ነው፡፡ የማከዳን ደስታ የፈጠረው የእዝራ የፍቅር አገላለፅ ሲሆን፤ ለእዝራ ልዩ ስሜት የፈጠረበት ደግሞ ተሰናብታው ልትሄድ ስትል የነበረው የማከዳ ቦይ አዘላለል ወይም እግር አነሳስ ሁኔታ ነው 😛 ) እንዲህ ሲል ይገልፀዋል...

"... የተኛ የመሰለ ቀኝ እግርዋ በአንዴ ነቅቶ ሲነሳ ....... ገና ተሻግሮ መሬት ከመንካቱ ጀርባዋ ለአመል ወደ ሁዋላ ሄዶ ሲመለስ..... ወገቧ ሊደርስ ዳር ዳር የሚለው ነዶ ፀጉሯ ጀርባዋን ሲለቅ..... ቀኝ እጅዋ እጄን ሳይለቅ ትቶኝ ሊሄድ ጣቶቼ ላይ ሲንሸራተት...... የስፖርተኛ ያልሆነ ግን የመሰለ አበለቃቀጧ........ ይሄ የእጆችዋ አዘረጋግ..... ልቦናዬ ሳይሻ እሷን በመልቀቁ ገፄ ላይ ሊኖር የሚችለው 'የአትሂጅብኝ' ቅሬታ...... እነዚህ ቀላል የመሰሉ ነገሮች ተጠረቃቅመው ለዘላለም እንድንኖር ወደ ነጭ የዕብነበረድ ሐውልት እንድንቀየር ተመኘሁ፡፡ " ...

እንዲህ አይነቱ አፃፃፍ "እንዲህ ተፈጥሮ፣ እንዲህ ተጉዞ፣ እንዲህ ሆኖ አለቀ፡፡" የሚል የአፃፃፍ ስልት ለሚወድና ለሚያደንቅ አንባቢ የሚያሰለች ሊሆን እንደሚችል ስጋቱ ቢሆንም፣ የታሪኩ ሂደት እምብዛም ለማያስጨንቀው አንባቢ ግን ይህ ነው የማይባል መመሰጥ እና አግራሞት ውስጥ መክተቱ የማይቀር ነው፡፡ ምክኒያቱም እነዚህ ቃላት እንደ ፈረስ ታሪክ ይዘው ሲጋልቡ አይስተዋሉም፤ ኩልል ብሎ እንደሚወርድ ፈሳሽ አንድን ድርጊት አሽሞንሙነው እና አጣፍጠው ለማቅረብ ሲተጉ እንጂ፡፡ እንደውም ይህንን የአፃፃፍ ስልቱን ደራሲው 'ታዚና' የተባሉትን ገፀ-ባህርይ ለማሳየት በተጠቀመበት መንገድ መልሼ ብገልፀው ደስ ይለኛል፡፡

"አንድ ነገር ሊናገር ሲፈልግ በዙርያ ጥምጥም ነው፡፡ ረዥም ክብ ሰርቶ የት መሄዱ ነው እየተባለ እየተጠረጠረ፣ ታሪክ ጠቅሶ፣ ተረት ተርቶ፣ ዞሮ ቁጭ ያደርጋል፡፡" .... እናም የአዳም የቃላት አሰካክ፣ የሀረጋት አወቃቀር፣ የዓ.ነገር አመሰራረት፣ የአንቀፆች ተጠየቃዊ የሀሳብ ፍሰትና መሰል ሁኔታዎች ደራሲው የቃላትም የጊዜም ሀብታም መሆኑን የሚያሳብቁ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ ወስዶኛል ....

**4. ገፀ-ባህርያት**

አራቱ ተራኪዎች (አላዛር፣ ተባረኪ፣ እዝራና ማከዳ) በምክንያት የተፈጠሩ፣ የየራሳቸው ወዝና ቀለም ያላቸው ድንቅ ገፀ-ባህርያት ቢሆኑም፣ የእይታቸው መነፅር ደርሶ የሚመሳሰልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ያስተውላሉ፣ ያሰላስላሉ፣ከምሽጋቸው ሆነው የማህበረሰቡን አይነኬ ጉዳዮች ሲመዙና ለጥያቄ ሲያቀርቡ ይስተዋላሉ... ወዘተ ...

ይህ የእይታ መነፅራቸው መመሳሰል በመረቅ ውስጥ ባሉ ገፀ-ባህርያት መሀል ብቻ የተፈጠረ ሳይሆን በሌሎች የደራሲው ስራዎች ውስጥ ካሉ ገፀ-ባህርያት ጋርም የተፈጠረ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ የቴቢ በዶሮ እግሮች መመሰጥ የግራጫ ቃጭሎቹን መዝገቡ ትውስታ ቀስቅሶብኛል፡፡ (ዘራፍ የአዳም ልጆች! የሚሉም ይመስለኛል 🙂 ደራሲው እንደ 'እዝራ' የተጠበበት ገፀ-ባህሪ ያለ ግን አይመስለኝም፡፡ አሳሳሉ "ዕፁብ ወዕፁብ ውእቱ/እስመ ለዕፁብ ትርጓሜ አልቦቱ" እንዳለው አይነት ነው ራሱ እዝራ ታዚና 🙂 ስለ እዝራ ምኑን ተናግሬ ምኑን ልተው እንግዲህ.....?

እዝራን ለእናንተ ልተውና ቅሬታ የተላበሰች አንዲት ትዝብቴን ላንሳ... በአዳም መፅሐፍ ውስጥ እንስቶቹ ከሚሰጣቸው ተመሳሳይ ሚና በተለየ መልኩ ተፅእኖ ፈጣሪ እንስት ገፀ-ባህርያትን የማየት ጉጉት ነበረኝ፤ አለኝም፡፡ ይህንን ጉጉቴን መረቅ ላይ ቴቢን አስነስቶ ሊያሳካው ነው ስል፣ ክንፏ የተሰበረ ወፍ አደረጋትና ምኞቴን ሁሉ ውሃ በላው፡፡

ቴቢ እንግዲህ "ከራስ በላይ ነፋስ በሚባለው ነገር አላምንም፡፡ ከራስ በላይ ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ሰፈር፣ ወረዳ፣ አውራጃ፣ ክፍለ ሃገርና አገር አሉ፡፡ የቻለበትም አህጉርና አለምን በልቦናው ይከታል፡፡"የሚል አቋም የነበራት፣ ይህንን ተቆርቋሪነቷንም በተግባር ለማሳየት እርምጃ የጀመረች ሴት ነበረች፡፡ ምንም እንኳን ይህንን አቋሟን በተግባር ለማሳየት የመረጠችው መንገድ ተገቢነት አጠያያቂ ቢሆንም ቴቢ መክሸፍ የነበረባት ገፀ-ባህሪ ናት ብዬ ግን አላምንም፡፡ አንድም ሳትከሽፍ በፊት ማዳን የሚቻልበት መንገድ መፍጠር ፤ ይህ ባይሆን እንኳን ያንን ሁሉ መንጋ የድርሳኗ ክፍል አለማድረግ ይቻላል የሚል አቋም አለኝ፡፡ ለምን ብባል እኔም እንደ ደራሲው ዘመን ተሻግረው ልናንቆለጳጽሳቸው የሚችሉ እንስት ገፀ-ባህርያትን በሀገራችን ሥነ-ፅሑፍውስጥ የማየት ጉጉት ስላለኝ ነው! ደራሲው ይህንን ክፍተት በ‹‹እቴሜቴ የሎሚ ሽታ›› ላይ አንስቶታል፤ የፍቅር እስከ መቃብሯን ሰብለ ወንጌልን (አንድ ለእናቷ) በየጊዜው ከመቃብር እያስነሳ የተለያየ ገፀ-ባህርይ ማላበሱም ይህንን ክፍተት የሚያጎላ ይመስለኛል፡፡ በበኩሌ ክፍተቱ በራሱ በደራሲው አማካኝነት ተሞልቶ የማየት ጉጉቴ አሁንም ድረስ እንዳለ ሳልገልፅ ማለፍ አልፈልግም፡፡

ከአራቱ ዋና ገፀ-ባህርያት በተጨማሪ ትኩረቴን ስለሳቡት ሌሎች አራት ገፀ-ባህርያት ደሞ ጥቂት ልበል ...

<u>ሮዛ</u> :የፊታውራሪ መሸሻ እና የወይዘሮ ጥሩ አይነት የልጅ ልጅ፤ የሰብለወንጌል መሸሻ ልጅ፤ የአላዛር ብርሃነ መስቀል እናት 🙂 ሳትናገር፣ ሳትጋገር በስራዋ ሁሉ ሰው የምታስደምም ደማሚት! እንደ ቴቢ አገላለፅ "የማይገባት የምትመስል ግን የምትሰራው ሁሉ በፍጹም የገባው አይነት፡፡"... የባሏ ሳይሆን የልጇ ግዴለሽነትና ናፍቆት ያቆሰላት፣ አቁስሎም የገደላት ምስኪን... አቤት አንጀት ስትበላ!

---

<u>ታዚና፡</u> የብሩህ አዕምሮ ባለቤት፣ ንግግራቸው ከተግባራቸው ጋር የሰመረላቸው፣ ከሰው ተርፈው ለንብ ሳይቀር የሚራሩና የሚሳሱ፣ በሰው ዘንድ ተሰሚነትና ተወዳጅነት ያላቸው መንፈሳዊ አባት...

<u>ብርሃነ መስቀል፡</u> በመፅሐፉ ውስጥ ብዙ የመናገር ዕድል አልተሰጠውም፤ ባገኛት አንዲት አጋጣሚ ግን እንዲህ አጀብ የሚያሰኝ ትዝብቱን ያካፍለናል፡፡ እንከተለውማ...

"... አገሪቷ አሁን ጥምዝምዝ ያለ የወሬ በሽታ ውስጥ ናት፡፡ 'ምሁሩ በመሰደድ ላይ ነው' ይላሉ፡፡ አገራችን ብዙ ምሁር የላትም የሚንጋጋም፡፡ የፖለቲካውን አለም ያሽከረክራሉ የሚባሉትን አንዳንዶቹን አውቃለሁ፡፡

ማከረር ይወዳሉ፡፡ በግድ ቼ ጉቬራን እንሁን ብሎ ነገር፡፡ አገሪቷ ቬትናም ብትሆን ደስ ይላቸዋል፡፡ ‘ለምን?’ ብትል ሆ ቺ ሚንን መሆን ይቀላቸዋል፡፡ ሌላው አለም ያሉ ግለሰቦች ጀግና የተባሉበትን ነገር ባያስፈልግም እዚህ ቢያደርጉ ደስ ይላቸዋል፡፡ በዚህ ብናደንቃቸው ይወዳሉ፡፡ ሺህ አይነት የአገርና የኢትዮጵያ ካባ ቢያለብሱት አንድ ነገር አውቃለሁ ቂል አይደለሁም I am not a fool. አንተም እንድትሆን አልፈልግም፡፡ በግድ ‘እንጣላ’ ብሎ ነገር ፍሊጋ አለ? ኢትዮጵያ ጠላቶቿ ላይ እንኳን አክራሪ አይደለችም፡፡ ሃይማኖታችንና ቋንቋችን የተዳቀለ ነው፡፡ ይሄ ልዩ ሊበራሊዝም ነው፡፡ የትም አገር የለም፡፡ ምን ማለት ነው? እንዲህ የሚያባላ ነገር የለም ማለት ነው፡፡ አንዳንድ አለባበስ አበላልን ምናምን የመሰለ ከባዕድ እንደሚቀዳ ልክ እንደ ጆሊ ጃኪዝም ምናምን በለው ፖለቲካውን.....፡፡ መተማማት መጋደልና መሰዳደብ አኮሳተረው እንጂ ውስጡ ያው ነው፡፡ የፖለቲካ ጆሊ ጃኮች፡፡ ወደ ፓስታ ሊለወጡ የሚለፉ ድፎ ዳቦዎች ናቸው፡፡ አሁን የማየውና የምሰማው ሁሉ ልክ አይደለም፡፡ አንድን ነገር ሳይመረምር በተራ ልዩነት ላይ ተመስርቶ ሺት የሚሰጥህ ገና ያላደገ ልጅ ነው፡፡ ያውም ሪታርድድ የሆነ፡፡ ልዩነትን በቋንቋ በማግነን በማይሆን ነገር ቶሎ ተገዳደድሎ መስዋዕት በመፍጠር የአላማ ነገር ተትቶ (ቀድሞም የለም) በነዚህ በፈጠሯቸው ሰማዕታት ስም ለዘላለም እንድንቀያየም የሚፈልጉ ይመስላል more shit will come::“ ...

<u>ሚሎስ፡</u> ጥያቄው፣ ምልከታው፣ ድምዳሜው ሁሉ ምክንያታዊ የሆነ ሰው ነው፡፡ ቀልቤን ከሳቡት ንግግሮቹ መሀል የተወሰኑትን ላካፍላችሁ፡-

“... ጥናት ከሌለ ዕውቀት የለም፡፡ ዕውቀት ከሌለ መለወጥ የለም፡፡ ልበ ሙሉነት ብቻውን ያለትክክለኛ መረጃ ምንም ነው፡፡ ሳታውቅ አውቀሃል ካሉህ አገልግሎትህ መስዋዕት መሆን ብቻ ነው፡፡ ማወቅ ሲገባህ ካላወቅህ ደደብ ነህ፡፡ ዕውቀትህ ስሜትን መቆጣጠር አለበት፡፡ ስሜት ዕውቀትን መያዝ/ማሰር የለበትም፡፡ የለውጥ ስሜትህን አይተው እሱንም ከዕውቀት አምታተው ሳታውቅ አውቀሃል ካሉህ፣ ጠላቶችህ ናቸው፡፡ ሹራቡ ላይ ጠላትህ ነኝ ብሎ ፅፎ እንዲመጣ ትጠብቃለህ? ...”

“... ሕይወት እኮ መለወጥ እንደምትችል በየጊዜው አንድ የተለየ ነገር እያደረክ ማረጋገጥ ነው፡፡ ማፍቀር እንደምትችል አረጋግጠሃል፡፡ መርሳት እንደምትችል አረጋግጥ፡፡ ይሄ የጣጣህን ፋይል ባንክ አድርገው፡፡ ከተመቸህና ከፈለክ ቀኑ ሲደርስ ፍሙን እየመዘዝክ ተቃጠል!”

**5. መውጪያ**

አብዛኞቹ ትረካዎች የሚቋጩት ልብ እንዳንጠለጠሉ ነው፡፡ ይህም ተደራሲው በድርሰቱ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚጋብዝ ነው ባይ ነኝ፡፡ ለምሳሌ፡ የማክዳ ትረካ የሚቋጨው በውድቅት ሌሊት የእዝራን ስም ስትጠራ ነው፡፡ ተደራሲው ቢፈልግ የአየር ጤናውን ጤናማ አየርና የሽሮሜዳውን አየር በዚህ የናፍቆት ጥሪ ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው በማድረግ ፍፃሜውን እንዳሻው ሊያሰማምረው ይችላል፤ ምነው ሸዋ! እንኳን ይሄንና እነ ሰብለወንጌልም ካሸለቡበት ነቅተዋል እኮ ....

በመጨረሻም ስለ እንጀራ ገለጣ ‹‹መግቢያ›› በሚል በመፅሐፉ መጨረሻ ላይ የሰፈረው ፅሁፍ ፋይዳ ግልፅ አልሆነልኝም እና የተገለጠለት ካለ ቢገልጥልኝ? ... እንደእኔ እንደእኔ ግን ስለ እንጀራ ገለጣ መግቢያ ከመስጠት ስለ ሕፅናዊነት የአፃፃፍ ስልት ነካ ነካ የተደረገውን የመውጫ ሀሳብ ቢገፋበት የሚል ቁጭት አሳድሮብኛል፡፡

... አበቃሁ...

***

የAdam Reta ምላሽ፡

I wish i could respond to you in Amharic but....my machine cannot handle that.
* The black and red cover.........'Altedegaagemem?'................

Did I use it elsewhere? Even if it is, there is no problem, and there is any symbolic meaning attached to them. There will be no transference of meaning (from Himmammatinna Begena) to here. I myself made the cover. I am the source. Precisely the book is the source. It is rather the map of the book, by taking those variables mentioned on the drawing. I found the lines plotting the values (page number, element....)

* About 'Injera Geletta'.......................................

It is an invented game. What i did was set few rules to create the impression of 'realty'. It is a 'hermeneutic play' or a game about interpretation. Mereq is both the form and content of things. We are sort of sediments of our experiences (private-social time). Sweet or not we are all Mereq.

If you want to have fun, you can lay on it......... and by the way, I have mentioned this in YESINBIT QELEMAT........ and there people not only play it.........they use it to predict the future............ so, in short, it is just fun.

Thank you Salome......... for your cool analysis and understanding.